# እስክንድር ጀግናችን

እልፍ ኦነግ ፣ እልፍ ኦሆዴድ ፣ ቢመዘኑ መጥተው
ተጨማሪ አስር ሺ ፣ መንጋን አሰማርተው
ቢሮክራሲያቸውን ፣ በጅምላ አካተው
ሚዛን እንዲያጋድል ፣ በቅማቸው ጎትተው
ኢትዮጵያዊነትን ፣ ሃቅን ያነገተው
አንድ እስክንድርን ሊሆን ፣ አልቻለም ያቃተው ።

እነ በልቶ አይጠግብ ፣ ዳቦ ፍሪዳቸው
እንኳንስ ከርሳቸው ፣ አይጠግብ አይናቸው
ከዳር አገር መጥተው ፣ ይሉኝታ የላቸው
አዲስ አበባችን ፣ ያስጎመጀቻቸው
አይውጧት አይተፏት ፣ ተቀርቅራባቸው
እያቁነጠነጠ ፣ እንቅልፍ የነሳቸው
ገና ስሙ ብቻ ፣ የሚያባንናቸው
ባላደራ አንበሳው ፣ ሆኗል ስጋታቸው ።

ጋንግሪን ተይዞ ፣ ሊያክም የሰው ቁስል
የራሱን በሽታ ፣ ሸሽጎ የሚያስመስል
የቤት እያረረ ፣ ጎርንቶ ሲከስል
መንደር እየዞረ ፣ ሰላምን የሚስል
ቁራው እርግብ ሆኖ ፣ ይታያል ሲያስመስል
የጎረቤቱን ወጥ ፣ ይውላል ሲያማስል ።

የኦነጉ አብይ ፣ መንጋን እየጠራ
ከሱሉልታ ፉሪ ፣ ጀሌ እያሳማራ
አስታጥቆ እየላከ ፣ ዱላና ገጀራ
በዱርዬ ስርአት ፣ ሐገርን ሊመራ
አይሞክረው የለም ፣ ይገፋል ተራራ
በዘኔ ይልካል ፣ ዜጋን ሊያስፈራራ ።

ኦነግ እርሾ ሆኖ ፣ ኦሆዴድ ተቦክቶ ፣ አብይን ቢጋግር
በሱሴ መደመር ፣ ያራዳ ግርግር
ያልሆነውን ሊሆን ፣ ቢዳክር ቢፎግር
መሆን አልተቻለም ፣ ታማኝ እንደ እስክንድር ።

እሰይ የኛ አንበሳ ፣ ንገሥ በልባችን
አንደራደርም ፣ በአዲስ አበባችን
ማንም አይነካትም ፣ አትወጣም ከጃችን
መቼም ወንድ አታጣም ፣ ሁሌም አገራችን
የምንሳሳለት ፣ እንዳይን ብሌናችን
የፅፈኛው ውጋት ፣ እስክንድር ጀግናችን ።

ታዛቢው

October 14, 2019